# መልክዐ አቡነ አባለ ክርስቶስ ጻድቅ (ዘአኀተሞ ገብረ ሥላሴ)

| መልክዐ አቡነ አባለ ክርስቶስ-ግዕዝ | የአቡነ አባለ ክርስቶስ ጻድቅ መልክዕ በአማርኛ |
|---|---|
| ፩. ንዑ ንኅሊ ማሕሌተ ለአባለ ክርስቶስ ጻድቅ፤ እለ ተጋባእነ ዮም እምነ ቅሩብ ወርሑቅ፤ ዘያደነግፆ ለፀር አባለ ክርስቶስ መብረቅ፤ ከመ ያንግፈነ እምእቶነ እሳት እሙቅ፤ በቃለ ኪዳን ዘነሥአ እም አምላክ ሊቅ፡፡ | 1. ንዑ ንኅሊ፡- ጠላትን የሚያስደነግጥ መብረቅ አባለ ክርስቶስ ከፈጣሪው በተቀበለው ቃል ኪዳን ከጥልቅ የእሳት ጉድጓድ እንዲያድነን ከሩቅና ከቅርብ የተሰበሰባችሁና የተሰባሰብን ኹላችን ዛሬ ኑ ለጻድቅ አባለ ክርስቶስ ምስጋና እናቅርብ፡፡ |
| ፪. ሰላም ለጽንሰትከ ወለልደትከ ብርሃን፤ ለአብ ወእም ምስለ ብዙኃን ጻድቃን፤ አባለ ክርስቶስ ጻድቅ ተወካፌ ጽኑዕ ኪዳን፤ አውኃዝከ ማየ ማሕየዌ ለመድኀኒተ ሰብእ ዱያን፤ አምጣነ ተውህበ ለከ ዘአምላክ ሥልጣን፡፡ | 2. ለጽንሰትከ፡- ከብዙ ጻድቃን ጋር ከአባትህና ከእናትህ ብርሃን ለሆነ መጸነስህና መወለድህ ሰላምታ ይገባል፤ ጽኑ ቃል ኪዳንን የተቀበልህ ጻድቅ አባለ ክርስቶስ ሆይ! የአምላክ ሥልጣን ተሰጥቶሃልና ለታመሙ ሰዎች መድኀኒት የሚሆን አዳኝ ውኃን አፈለቅህ፡፡ |
| ፫. ሰላም ለዝክረ ስምከ ስቡሐ ዘተሰብሐ፤ በአፈ መላእክት ወሰብእ እለ ያፈቅሩ ንጽሐ፤ አባለ ክርስቶስ ዜናከ ውስተ አጽናፈ ምድር ዘበጽሐ፤ ይገብሩ ሕዝብ በዓለከ በተአ ምኖ ብዙኀ፤ ምስለ በዓለ ሊቅ ገብርኤል ዘኮነ አሚሃ፡፡ | 3. ለዝክረ ስምከ፡- ንጽሕናን የወለዱ በመላእክትና በሰው አንደበት ለተመሰገነ ለስምህ መታሰቢያ ሰላምታ ይገባል፤ አባታችን አባለ ክርስቶስ ሆይ! ዜናህ ወደ ዓለም ዳርቻ ደርሷልና ከሊቀ መላእክት ከቅዱስ ገብርኤል በዓል ጋር በሆነ ጊዜ በብዙ መታመን ምእመናን በዓልህን ያከብራሉ፡፡ |
| ፬. ሰላም ለሥዕርተ ርእስከ ዘኁላቌሁ ተዐውቀ፤ በልበ ሥላሴ ነገሥት እለ ያፈቅሩከ ጥቀ፤ አባለ ክርስቶስ መናኒ እንተ ኢታፈቅር ወርቀ፤ ያመጽኡ ለከ አምኀ እለ የኀሥሡ ጽድቀ፤ እስመ ውስተ ኵሉ ዓለም ዜናከ አልጸቀ፡፡ | 4. ለሥዕርተ ርእስከ፡- እጅግ በሚወዱህ በገዥዎች ሥላሴ ልብ ቍጥሩ ለታወቀ ለራስህ ጠጕር ሰላምታ ይገባል፤ ወርቅን የማትወድ መናኝ አባታችን አባለ ክርስቶስ ሆይ! ወደ ዓለም ኹሉ ዜናህ ደርሷልና ጽድቅን የፈለጉ ኹሉ እጅ መንሻ ያመጡልሃል፡፡ |
| ፭. ሰላም ለርእስከ እንተ ክርስቶስ ርእሱ፤ በከመ ተሰምየ ርእሰ ለቤተ ክርስቲያን መቅደሱ፤ አባለ ክርስቶስ ዘኮንከ ሕይወተ ሥጋሁ ወነፍሱ፤ ለዘሐመ ሰብእ መዋቲ በሕማመ ሥጋ እምንእሱ፤ ውስተ መቅደስከ ነዐ ምስሌነ ታንሶሱ፡፡ | 5. ለርእስከ፡- ለመመስገኛው ቤተ ክርስቲያን ራስ ተብሎ እንደተጠራ ክርስቶስ አለቃው ለሆነ ራስህ ሰላምታ ይገባል፤ በነፍሱና በሥጋው ከታናሽነቱ ጀምሮ ታሞ ለሞተ የሥጋውና የነፍሱ ሕይወት የሆንህ አባለ ክርስቶስ ሆይ! ከእኛ ጋር ትኖር ዘንድ ወደ መቅደስህ ና፡፡ |

| | |
|---|---|
| ፮. ሰላም ለገጽከ ዘአስተርአየ በገጽ፤ እግዚአብሔር ዘገብረ መድኀኒተ ዓለም በዕፅ፤ አባለ ክርስቶስ ኖላዊ ቤዛ አባግዕ አብያጽ፤ መራሔ ኩነነ አሚሃ ለዕለተ ብዙኅ ተግሣፅ፤ እስመ ፍና ሕይወት አንተ ወዘጽድቅ አንቀጽ፡ | 6. ለገጽከ፡- የዓለምን መድኀኒት በዕንጨት የአደረገ እግዚአብሔር በፊት ለታየው ፊትህ ሰላምታ ይገባል፤ የወዳጆች በጐች ቤዛ የሆንህ እረኛ አባለ ክርስቶስ ሆይ! አንተ የእውነት በርና የሕይወት ጐዳና ነህና በብዙ መከራ ቀን ያን ጊዜ መሪ ሁነን፡፡ |
| ፯. ሰላም ለቀራንብቲከ ዘበማየ አንብዕ ተሐጽባ፤ በከመ ትቤ ወንጌል ዘይትረከብ ጥበባ፤ አባለ ክርስቶስ ዘፆርከ በውስተ ዓለም አፀባ፤ በእንተ ሰላም ለመቅደስከ በመርሕባ፤ ከመ በረከትከ እንሣእ ባርከኒ አባ፡፡ | 7. ለቀራንብቲከ፡- ጥበቧ የሚመረመር ወንጌል እንደተናገረች በዕንባ ውኃ ለታጠቡ ቅንድቦችህ ሰላምታ ይገባል፤ በዓለም ውስጥ መከራን የተሸከምህ አባለ ክርስቶስ ሆይ! ስለ መቅደስህ ዐደባባይ ሰላም በረከትህን እቀበል ዘንድ አባት ሆይ! ባርከኝ፡፡ |
| ፰. ሰላም ለአዕይንቲከ እለ ያነብኣ ወትረ፤ በእንተ ርእሶን ቅድመ ወበእንተ ኃጥኣን ድኅረ፤ አባለ ክርስቶስ ዘኮንከ ዘእግዚአብሔር ማኅደረ፤ ንስእለከ ይእዜ ወናስ ተበቍዓከ ምዕረ፤ ከመ ትኩነነ ለነ ዘመስቀል ሐፁረ፡፡ | 8. ለአዕይንቲከ፡- ስለ ራሳቸው በማስቀደም በኋላም ስለ ኀጢአተኞች ሁልጊዜ ለሚያነቡ ዐይኖችህ ሰላምታ ይገባል፤ የእግዚአብሔር ማደሪያ የሆንህ ቅዱስ አባታችን አባለ ክርስቶስ ሆይ! ለእኛ እንደ መስቀል አጥር ትሆን ዘንድ ዛሬ እንለምንሃለን፤ በእጅጉም እንማልድሃለን፡፡ |
| ፱. ሰላም ለአእዛኒከ እለ ያፀምኣ ቃለ፤ ዘበውስተ ወንጌል ተብህለ፤ አባለ ክርስቶስ አቡነ እንተ አፈድፈድከ ገድለ፤ ንስእለከ ይእዜ ከመ ትርዳእ ዘተኀጕለ፤ ወዘተመዝበረ ትሕንጽ ነሚአከ ኀይለ፡፡ | 9. ለአእዛኒከ፡- በወንጌል ውስጥ እንደተነገረ ቃልን ለሚያዳምጡ ጆሮዎችህ ሰላምታ ይገባል፤ ተጋድሎን የአበዛህ አባታችን አባለ ክርስቶስ ሆይ! የጠፋውን ትረዳ ዘንድ ኀይልን ተቀበልህ፤ የፈረሰውን ትሠራ ዘንድ ዛሬ እንማልድሃለን፡፡ |
| ፲. ሰላም ለመላትሒከ እለ ያውኀዛ ሐፈ፤ እንዘ ውስተ ምድር ትሰግድ ከመ ትፈጽም ጽሑፈ፤ አባለ ክርስቶስ ሥጋከ አመ ዕድሜሁ ኃለፈ፤ ወረዱ ይትቀበሉከ እለ ተሰምዩ አእላፈ፤ እንዘ ይትጓድዑ በአክናፍ አክናፈ፡፡ | 10. ለመላትሒከ፡- የተጻፈውን ትፈጽም ዘንድ ወደ ምድር እየሰገድህ ወዝን ለአፈሰሱ ጉንጮችህ ሰላምታ ይገባል፤ አባታችን አባለ ክርስቶስ ሆይ! ሥጋህ ዕድሜው ባለፈ ጊዜ አእላፍ የተባሉ ይቀበሉህ ዘንድ ክንፋቸውን ከክንፋቸው እያማቱ ወረዱ፡፡ |
| ፲፩. ሰላም ለአእናፊከ እለ አጼነዋ ጼና፤ እንተ ይመስጥ ልቡና፤ ፀዋሬ ምሕረት ዝናም አባለ ክርስቶስ ደመና፤ አዝንም ለነ ይእዜ ዝናመ ሕዋሳት ጥዒና፤ ከመ በግብርከ ንርከብ ልምላሜ ልዕልና፡፡ | 11. ለአእናፊከ፡- ልብን የሚመስጥ መናን ለአሸተቱ አፍንጫዎችህ ሰላምታ ይገባል፤ የምሕረት ዝናምን የያዝህ ደመና አባለ ክርስቶስ ሆይ! በሥራህ ከፍታ ልምላሜን እናገኝ ዘንድ የሰውነት ጤና ዝናምን ዛሬ አዝናም፡፡ |

| | |
|---|---|
| ፲፪. ሰላም ለከናፍሪከ እለ ነበባ ስብሐተ፤ አምሳለ ጎሩይ ገብርኤል ዘተወፈየ ብሥራተ፤ አባለ ክርስቶስ አቡነ ዘአፈድፈድከ ጸሎተ፤ ተጋደልከ ገድለ በኵሉ እንዘ ታበዝኅ ትዕግሥተ፤ ለመንግሥተ ሰማይ ትሕንፅ ዘብርሃን አብያተ፡፡ | 12. ለከናፍሪከ፡- የምሥራችን እንደ ተቀበለ እንደ ተመረጠ ገብርኤል ምስጋናን ለተናገሩ ከንፈሮችህ ሰላምታ ይገባል፤ ጸሎትን ያበዛህ አባታችን አባለ ክርስቶስ ሆይ! በመንግሥተ ሰማይ የብርሃን ቤቶችን ትሠራ ዘንድ ትዕግሥትን እያበዛህ በኹሉ ቦታ መጋደልን ተጋደልህ፡፡ |
| ፲፫. ሰላም ለአፉከ ወንጌለ ዘሰአመ፤ እንዘ ይነብብ ሰላመ፤ አባለ ክርስቶስ ምስሌከ ቃለ መሐላሁ ፈጸመ፤ እግዚአብሔር ሕያው በማኅበረ ጻድቃን ዘቆመ፤ ከመ ያድኅን በጸውዖ ዘኢአከ ስመ፡፡ | 13. ለአፉከ፡- ሰላምን እየተናገረ ወንጌልን ለተሳለመ አፍህ ሰላምታ ይገባል፤ አባታችን አባለ ክርስቶስ ሆይ! ስምህን የጠራውን ኹሉ ያድን ዘንድ በጻድቃን ማኅበር የቆመ ሕያው እግዚአብሔር ከአንተ ጋር ቃል ኪዳኑን ፈጸመ፡፡ |
| ፲፬. ሰላም ለአስናኒከ እለ ይመስላ ሀሊበ፤ ዘበግብረ አምላክ ተረክበ፤ አባለ ክርስቶስ የዋህ አንተ ተመሰልከ ርግበ፤ እፎኑመ ኮንከ በኵሉ ከመ አርዌ ምድር ጠቢበ፤ በከመ ይቤ ወንጌል ዘለከ ተውህበ፡፡ | 14. ለአስናኒከ፡- በአምላክ ሥራ የተገኘ ወተትን ለሚመስሉ ጥርሶችህ ሰላምታ ይገባል፤ በርግብ የተመሰልህ የዋህ አባለ ክርስቶስ ሆይ! ለአንተ የተሰጠ ወንጌል እንደተናገረ በኹሉ እንደ ምድር አውሬ ጥበበኛ ሆንህ፡፡ |
| ፲፭. ሰላም ለልሳንከ እንተ ይሴብሕ አምላከ፤ ኵሎ ዓለመ ዘበሥልጣኑ መለከ፤ አባለ ክርስቶስ ዮሐንስ ወንጌለ መለኮት ሰበከ፤ አኮኑ ከመ ጥበ ላህም ጥበብ ሐፀነተከ፤ ወለልቡና መካነ በምሥጢር ኮንከ፡፡ | 15. ለልሳንከ፡- ዓለምን ኹሉ በሥልጣን የገዛ አምላክን ለሚያመሰግን አንደበትህ ሰላምታ ይገባል፤ የመለኮትን ወንጌል የአስተማርህ ዮሐንስ አባለ ክርስቶስ ሆይ! ጥበብ እንደ ላም ጡት አሳድጋሃለችና በማስተዋልም ምሥጢር ማደሪያ አደረገችህ፡፡ |
| ፲፮. ሰላም ለቃልከ ዘኢተሰምዐ በዕዝን፤ እንዘ ንብረቱ ውእቱ በውስተ ኅቡዕ መካን፤ ዐቃቤ ሥራይ ዘኮንከ አባለ ክርስቶስ መድኅን፤ ፈውሰኒ ወአሕይወኒ እምሕማመ ርእሰ ወዐይን፤ አምጣነ ኵሎ ትፌውስ በአዚዝ ሥልጣን፡፡ | 16. ለቃልከ፡- መኖሪያው በተሠወረ ቦታ ሲሆን በጆሮ ለአልተሰማ ቃልህ ሰላምታ ይገባል፤ ባለ መድኀኒት የሆንህ መድኅን አባለ ክርስቶስ ሆይ! በሚቻል ሥልጣን ኹሉን ትፈውሳለህና ከዐይንና ከራስ ጽኑ ሕማም ፈጽመህ አድነኝ፡፡ |
| ፲፯. ሰላም ለእስትንፋስከ አምሳለ እፍረት ምዑዝ፤ ዘይመስጥ ልበ እንተ አልቦቱ ትካዝ፤ አባለ ክርስቶስ መልአክ ፈጻሚ ብዙኅ ትእዛዝ፤ ዕቀበኒ እምነ ፀር ወአድኅነኒ እምጋዕዝ፤አምጣነ ኵሎ ታድኅን በሥልጣን አዚዝ፡፡ | 17. ለእስትንፋስከ፡- ኀዘን የሌለውን ልብ የሚመስጥ እንደ ሽቱ ለሚጣፍጥ እስትንፋስህ ሰላምታ ይገባል፤ ሕግን የምትፈጽም መልአክ አባለ ክርስቶስ ሆይ! በከበረ ሥልጣን ኹሉ ታድናለህና ከጠላት ጠብቀኝ፤ ከጥላቻም አድነኝ፡፡ |

| | |
|---|---|
| ፲፰. ሰላም ለጕርዔከ እንተ አፈድፈደ ጽምአ፤ ከመ በቀኖና ሕጎሙ ለመነኰሳት ተሠርዐ፤ አባለ ክርስቶስ ፈጸምከ ትሩፋተ ውስጥ ወአፍኣ፤ እስመ ተመሰልከ አንበሳ ዘሞአ፤ ወእምጕንደ ዳዊት ዘይሁዳ ዘረከበ ዘርዐ፡፡ | 18. ለጕርዔከ፡- በመነኰሳት ሕግ በቀኖና እንደተሠራ መጠማትን ለአበዛ ጕሮሮህ ሰላምታ ይገባል፤ አቡነ አባለ ክርስቶስ ሆይ! የውስጥና የውጪ ትሩፋትን ፈጽመህ አሸናፊ አንበሳን መስለሃልና ከይሁዳ ወገን ዳዊት ባሕርይ ዘርን አገኘ |
| ፲፱. ሰላም ዕብል ለክሣድከ ቢረሌ፤ ዘምሉዐ ኮነ ወይነ መላእክት ሃሌ፤ አባለ ክርስቶስ መምህር ዘለጳውሎስ ምሳሌ፤ ሠርዌሆሙ ለተባሕትዎ ወዘዮሐንስ ድንጋሌ፤ እስመ አበ አእላፍ አንተ በብዙኀ ትንባሌ፡፡ | 19. ለክሣድከ፡- የመላእክት ምስጋና ወይንን የተመላ ለሆነ ለቢረሌ አንገትህ ሰላምታ ይገባል፤ የጳውሎስ ምሳሌ መምህር አባለ ክርስቶስ ሆይ! በብዙ ልመና አንተ የብዙዎች አባት ነህና ለዮሐንስ ለተሰጠው ድንግልናና ለብሕትውና አለቃ ሆንህ፡፡ |
| ፳. ሰላም ለመትከፍትከ እንተ ይፀውር በግአ፤ ዘበውስተ ገዳም ጠፍአ፤ አባለ ክርስቶስ ሥርግው ዘለበስከ ልብስ መርዓ፤ አልብስኒ ልብሰ ዚኣከ ከመ ኢይኩን ውጹአ፤ እመንግሥተ ሰማይ ቤትከ ውስተ ሐቅል አፍኣ፡፡ | 20. ለመትከፍትከ፡- በበረሓ ውስጥ የጠፋ በግን ለተሸከመ ትከሻህ ሰላምታ ይገባል፤ የሙሽራ ልብስን የለበስህ የተሸለምህ አባለ ክርስቶስ ሆይ! ከበረሓ ውጭ የሆነ ከመንግሥተ ሰማይ ቤትህ የወጣሁ እንዳልሆን ለልጅህ ልብስህን አልብሰኝ፡፡ |
| ፳፩. ሰላም ለዘባንከ እንተ ዕብን ምስማኩ፤ ከመ ለልየርኢኩ፤ አባለ ክርስቶስ ክቡር ለእግዚአብሔር መልአኩ፤ ተወከፍ ሊተ ጸሎትየ ሶበ ኀቤከ ጸራሕኩ፤ እስመ ጸሎተከ አንሰ ፀወነ ረሠይኩ፡፡ | 21. ለዘባንከ፡- እኔ እንደ አየሁት መጠጊያው ድንጋይ ለሆነ ጀርባህ ሰላምታ ይገባል፤ የእግዚአብሔር መልእክተኛ የከበርህ ቅዱስ አባታችን አባለ ክርስቶስ ሆይ! ጸሎትህን እኔ መጠጊያ አድርጌአለሁና ወደ አንተ በጮህሁ ጊዜ ጸሎቴን ተቀበልልኝ፡፡ |
| ፳፪. ሰላም ለእንግድዓከ በብዙኅ አዕምሮ፤ ዘይፀውር ዘልፈ ለእግዚአብሔር ምሥጢሮ፤ አባለ ክርስቶስ ትጉት እንተ አልብከ ተዝሕሮ፤ መምህራን አዘዙ እንዘ ይብሉ ለአባለ ክርስቶስ ተዝካሮ፤ ግበሩ በፍሥሓ ወምሩ ዘምሮ፡፡ | 22. ለእንግድዓከ፡- በብዙ ዕውቀት ሁልጊዜ የእግዚአብሔርን ምሥጢር ለተሸከመ ደረትህ ሰላምታ ይገባል፤ ትዕቢት የሌለህ ትጉት አባታችን አባለ ክርስቶስ ሆይ! ‹የአባለ ክርስቶስን መታሰቢያ በደስታ አድርጉ፤ ምስጋናንም አመስግኑ› እያሉ መምህራን አዘዙ፡፡ |
| ፳፫. ሰላም ለሕፅንከ እንተ ኬንያሁ አምላክ፤ ለቡርክት እምከ በውስተ ከርሣ ቡሩክ፤ አባለ ክርስቶስ ጸሊ ኀበ አምላክ፤ በምድረ ጽዮን ማኅበርነ ኢይኩን ሐከክ፤ ወበገራህታ ልብነ ኢይብቍል ሦክ፡፡ | 23. ለሕፅንከ፡- በተባረከች እናትህ በተባረከ ማሕፀኗ ውስጥ አምላክ ለተጠበበበት እቅፍህ ሰላምታ ይገባል፤ አባታችን አባለ ክርስቶስ ሆይ! በምድረ ጽዮን ማኅበራችን ክርክር እንዳይሆን በእርሻዋ ልባችንም እሾህ እንዳይበቅል ወደ አምላክ ጸልይ፡፡ |

| | |
|---|---|
| ፳፬. ሰላም ለአእዳዊከ እለ ስፉሐት ለጸልዮ፤ ኀበ እግዚእከ ወልድ ዘተሰብሐ በቀራንዮ፤ አባለ ክርስቶስ ንጹሕ እንተ አልብከ ጌግዮ፤ በነፍስየ ዐጸደ ወይን አስተባዛኀከ ተቀንዮ፤ ወለለጊዜሁ ይእቲ ትፈቅድ ተሰቅዮ፡፡ | 24. ለአእዳዊከ፡- በቀራንዮ የተመሰገነ ወደ ጌታህ እግዚአብሔር ወልድ ለመጸለይ ለተዘረጉ እጆችህ ሰላምታ ይገባል፤ በደል የሌለብህ ንጹሕ አባለ ክርስቶስ ሆይ! እርሷ በየጊዜው ውኃ መጠጣት ትፈልጋለችና በነፍሴ የወይን ቦታ መገዛትን አበዛህ፡ |
| ፳፭. ሰላም ለመዛርዒከ እለ ኮኑ ጽኑዓነ፤ በዲበ ሠናይ ኮንኮሙ ይትዋሰኡ ለነ፤ አባለ ክርስቶስ ዘኮንከ ለነፍሰ ኃጥኣን ፀወነ፤ አዕትቶ ለሕማምየ ወጸግወኒ ብርሃነ፤ እስመ እምኢ.ርእየ ዐይን ኢ.ይከውን ዓይነ፡፡ | 25. ለመዛርዒከ፡- በበጐ ነገር ለእኛ እንዲመልሱልን የበረቱ ለሆኑ መከንጃዎችህ ሰላምታ ይገባል፤ ለኀጢአተኞች ነፍሳት መጠጊያ የሆንህ አባለ ክርስቶስ ሆይ! ዐይን ከአላየ ዐይን አይሆንምና ጽኑ ደዌዬንና ሕማምዬን አስወግደው፤ ብርሃንንም ስጠኝ፡ |
| ፳፮. ሰላም ለኵርናዕከ ዘበተጋድሎ ተግህደ፤ ምንዳቤ ወጻዕረ እንዘ ይትዌከፍ ፈድፋደ፤ አባለ ክርስቶስ ዘኮንከ ፈላሴ ወነግደ፤ በመንክራቲከ ኀይለ ደዌ ተሰደ፤ ጸጋ መንፈስ ቅዱስ ላዕሌከ አኮኑ ወረደ፡፡ | 26. ለኵርናዕከ፡- ጭንቅንና ችግርን እጅግ እየተቀበለ በመጋደል ለተገለጠ ክርንህ ሰላምታ ይገባል፤ እንግዳና መጻተኛ የሆንህ አባለ ክርስቶስ ሆይ! የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ በአንተ ላይ ወርዷልና በተኣምራትህ የደዌ ኀይል ተሰደደ፡፡ |
| ፳፯. ሰላም ለእመትከ ዘእመተ አዳም መጠኑ፤ በከመ ይቤ መጽሐፍ ዘበዐውደ ጽድቅ ትዜኑ፤ አባለ ክርስቶስ ላእሌነ ጸጋ መንፈስ ቅዱስ ፈኑ፤ በገድለ ፃማከ እንተ ይትአወቅ ሥልጣኑ፤ ለቤዛ ኵሉ ዐፅምከ ዘመንክር ኪኑ ፡፡ | 27. ለእመትከ፡- በጽድቅ ዐደባባይ የሚናገር መጽሐፍ እንደተናገረ የአዳም ክንድ ልኩ ለሆነ ክንድህ ሰላምታ ይገባል፤ አባታችን አባለ ክርስቶስ ሆይ! የመንፈስ ቅዱስ ጸጋን በላያችን ላክ፤ ሥልጣኑ በሚታወቅ በመጋደልህ ድካም ጥበቡ የሚያስደንቅ ዐፅምህ ለኹሉ ቤዛ ነው፡፡ |
| ፳፰. ሰላም ለእራኀከ ስፉሐ ላዕሉ ወታሕቴ፤ በሰአተ ሞት መፍርህ አዕይንቲከ ክልኤቴ፤ አባለ ክርስቶስ ኀሩይ ወለመንፈስ ቅዱስ ታቦቴ፤ ዘመነ ዚኣየ ለእመ ሐልቀ በከንቴ፤ ቤዛ ይኩነኒ ጸሎትከ ዝንቴ፡፡ | 28. ለእራኀከ፡- በሚያስፈራ ሞት ጊዜ ከኹለቱ ዐይኖችህ ጋር ወደላይና ወደታች ለተዘረጉ መሐል እጆችህ ሰላምታ ይገባል፤ የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ የተመረጥህ አባለ ክርስቶስ ሆይ! ዘመኔ በከንቱ ቢያልቅም ይኽ ጸሎትህ ቤዛ ይሁነኝ፡፡ |
| ፳፱. ሰላም ለአጻብዒከ ዘአርአያሁ ሠናይ፤ በከመ ይቤ ነቢይ፤ ብርሃነ ዓለም ዘኮንከ አባለ ክርስቶስ ፀሐይ፤ ሶበ ሠረቀ በምሥራቅ ጽልመተ ልቡና ጌጋይ፤ እመካነ ልብ ተስደ በብርሃን ውኩይ፡፡ | 29. ለአጻብዒከ፡- ነቢይ እንደተናገረ መልኩ ለአማረ ጣትህ ሰላምታ ይገባል፤ የዓለም ብርሃን የሆንህ አባለ ክርስቶስ ሆይ! ፀሐይ በምሥራቅ በወጣ ጊዜ የልብ በደል ጨለማ ከልብ ቦታ በበራ ብርሃን ተሰደደ፡፡ |

| | |
|---|---|
| ፴. ሰላም ለአጽፋረ እዴከ ዘኀበሪሁ ብርሃነ ፍግዕ፤ በሥምረተ አምላክ እግዚእ፤ አባለ ክርስቶስ ታቦት በቅብዐ ሜሮን ቅቡዕ፤ ንሰግድ ለከ በኵሉ ማዕዘነ መቅደስ አርባእ፤ አምጣነ ኃደረ ብከ መለኮት ጽኑዕ፡፡ | 30. ለአጽፋረ እዴከ፡- በጌታ አምላክ ፈቃድ መልኩ የሚያስደስት ብርሃን ለሆነ ለእጅህ ጥፍሮች ሰላምታ ይገባል፤ በሜሮን ቅባት የተቀባህ ታቦት አባለ ክርስቶስ ሆይ! የጸና መለኮት አድሮብሃልና በአራቱ መዓዘነ መቅደስህ ለአንተ እንሰግዳለን፡፡ |
| ፴፩. ሰላም ለገቦከ እንተ ኢሠምረ ምስካቦ፤ ለገቦ ረሲአን አብዳን መንጸፈ ኪሩብ ዘአልቦ፤ አባለ ክርስቶስ ክብርከ ዕፁብ ለተናብቦ፤ ማኅበረነ ባርክ በእዴከ ወበእዴከ ጸልቦ፤ እስመ በመስቀልከ ንሕነ ንፈቱ ተዐቅቦ፡፡ | 31. ለገቦከ፡- የኪሩቤል ምንጣፍ የሌለው የሰነፎች ጐስቋሎች መኝታን ለአልወደደ ጐንህ ሰላምታ ይገባል፤ አባታችን አባለ ክርስቶስ ሆይ! ክብርህ ለመናገር ድንቅ ነው፤ እኛ በመስቀልህ መጠበቅ እንፈልጋለንና ማኅበራችንን በእጅህ መስቀል ባርክ፡፡ |
| ፴፪. ሰላም ለከርሥከ ዘትጋሃ ጸሎት መዝገብ፤ ጽጌ ስርየተ ነፍስ ትቀስም እምሐቅለ ራትዓን አብ፤ ለገቢረ ሕይወት መዓር አባለ ክርስቶስ ንህብ፤ እስመ ኮንከ ጥዑመ ምግባር በዘመንፈስ ቅዱስ ጥበብ፤ ወጣዕመ ትንባሌከ ጸቃውዕ ለአብዳን ሕዝብ፡፡ | 32. ለከርሥከ፡- አብ ከመረጣቸው ጻድቃን በረሓ የነፍስ ስርየት አበባን ትለቅም ዘንድ የጸሎት ትጋት መገኛ ለሆነ ሆድህ ሰላምታ ይገባል፤ ሕይወት ማርን ለመሥራት ንብ የሆንህ አባታችን አባለ ክርስቶስ ሆይ! በመንፈስ ቅዱስ ጥበብ ሥራህ የሚያስደስት ሆነሃልና ለሰነፎች ሰዎችም የአማላጅነትህ ጣዕም ወለላ ነው፡፡ |
| ፴፫. ሰላም ለልብከ እንተ አልቦቱ በቀል፤ እንበለ ርኅራኄ ወሣህል፤ ዘሙሐዘ ጸሎት ሰተይከ አባለ ክርስቶስ ተክል፤ ፍሬ ክብር ትፈሪ ለኵሉ በዓመተ ምሕረት ገድል፤ እንዘ ኢይትነገፍ ላዕለ ምድር ትንባሌከ ቆጽል፡፡ | 33. ለልብከ፡- ከርኅራኄና ከይቅርታ በቀር በቀል ለሌለው ልብህ ሰላምታ ይገባል፤ የጸሎት ፈሳሽ ምስጋናን የጠጣህ ተክል አባለ ክርስቶስ ሆይ! ምልጃህ ቅጠል ወደ ምድር ሳይወድቅ በመጋደል የምሕረት ዓመት የክብር ፍሬን ለኹሉ ታፈራለህ፡፡ |
| ፴፬. ሰላም ለኵልያቲከ አንቀጸ ጥበብ መንፈሳዊ፤ በከመ ይቤ ወንጌላዊ፤ ዘበአንቀጸ ገድል ትበውእ አባለ ክርስቶስ ኖላዊ፤ ለአባግዒከ ነገደ ይሁዳ ወሌዊ፤ ዕቀበነ በትጋህ እምአርዌ ነዓዊ፡፡ | 34. ለኵልያቲከ፡- ወንጌላዊ እንደተናገረ የመንፈሳዊ ጥበብ በር ለሆኑ ኵላሊቶችህ ሰላምታ ይገባል፤ በመጋደል በር የምትገባ ጠባቂ አባለ ክርስቶስ ሆይ! የይሁዳና የሌዊ ወገን በጐችህን ከአዳኝ አውሬ በትጋት ጠብቀን፡፡ |
| ፴፭. ሰላም ለኅሊናከ ካልአ ዘኢይኄሊ፤ እንበለ ዳዕሙ ጸሎተ በበጊዜሁ ይጼሊ፤ ሥቃያተ ረኀብ ወጽምዕ አባለ ክርስቶስ ከሐሊ፤ ሥጋሁ ለሰብእ አእሚረከ ከመ ይማስን ወይበሊ፤ በተጋድሎ አምሰጥከ | 35. ለኅሊናከ፡- ጸሎትን በየጊዜው ይጸልዩ ዘንድ ነው እንጂ ሌላ ነገርን ለማያስብ ኅሊናህ ሰላምታ ይገባል፤ የረኀብንና የጥማትን መከራ የምትችል አባታችን አባለ ክርስቶስ ሆይ! የሰው ሥጋ እንደሚጠፋ እንደሚያረጅ ዐውቀህ ከሚያጠፋ ክፉ ነገር በመጋደል አመለጥህ፡፡ |

| | |
|---|---|
| እምእኩይ ማኀኮሊ፡፡ | |
| ፴፮. ሰላም ለአማዑቲከ ፀዋሬ ምሥጢር ስፉሕ፣ አምሳለ መዝገቡ ለዮሴፍ ወአምሳለ ታቦት ዘኖኅ፣ አባለ ክርስቶስ ምርሐነ በማኅቶትከ ብሩህ፣ ከመ ንባእ ምልእተ ዋካ ጽርሐ መርዓዊ ንጹሕ፣ አምጣነ ለገብር ኄር እሴቱ ብዙኅ፡፡ | 36. ለአማዑቲከ፡- በኖኅ ታቦትና በዮሴፍ መዝገብ አምሳያ በዚኽ ምሥጢርን ለተሸከመ አንጀትህ ሰላምታ ይገባል፣ አባታችን አባለ ክርስቶስ ሆይ! ብርሃንን ወደተመላች የንጹሕ ሙሽራ አዳራሽ እንገባ ዘንድ በብሩህ ብርሃንህ ምራን፣ የታማኝ ባሪያ ዋጋው ብዙ ነውና፡፡ |
| ፴፯. ሰላም ለንዋየ ውስጥከ ከመ እንተ ባሕርይ ሥሙር፣ በኀበ ሥሉስ ቅዱስ ወበኀበ ኵሉ ፍጡር፣ ዘአስበ ፃማ ተአሲ አባለ ክርስቶስ መምህር፣ ሀቦሙ አስበ ፃማሆሙ ለሰብእ ዛቲ ሀገር፣ እስመ ተዘካረከ ገብሩ በሰላም ወፍቅር፡፡ | 37. ለንዋየ ውስጥከ፡- በሥሉስ ቅዱስ እና በፍጡር ኹሉ ዘንድ እንደ ዕንቁ ለተወደደ ሆድ ዕቃህ ሰላምታ ይገባል፣ የድካምን ዋጋ የምትከፍል መምህር አባለ ክርስቶስ ሆይ! በሰላምና በፍቅር መታሰቢያህን አድርገዋልና ለዚኽች ሀገር ሰዎች የድካማቸውን ዋጋ ስጣቸው፡፡ |
| ፴፰. ሰላም ለኅንብርትከ ዘበውስተ ማእከል ሀለወ፣ በኀበ ኵሉ ዘነፍስ እንዘ ይከውን ፍትወ፣ አባለ ክርስቶስ ዘኮንከ ምስለ ገብርኤል ስንዕወ፣ ለዘገብረ ተዝካረከ ዘበቃለ ኪዳን ርኅወ፣ ኆኅተ ገነት አርኃውከ ወኮንከ ድልወ፡፡ | 38. ለኅንብርትከ፡- በሰውነት ኹሉ የተወደደ ሲሆን በአካል ውስጥ ለአለ እምብርትህ ሰላምታ ይገባል፣ ከቅዱስ ገብርኤል ጋር የተስማማህ የሆንህ አባለ ክርስቶስ ሆይ! በቃል ኪዳን የከበረ መታሰቢያህን ለአደረገ የገነትን በር ከፈትህ፣ የተዘጋጀህም ሆንህ፡፡ |
| ፴፱. ሰላም ለሐቋከ መዋባሕተ ቅዱሳን መከራ፣ ዘይቀንት ዘልፈ በውሳጤ ገዳም ደብተራ፣ አባለ ክርስቶስ ይብሉከ ሰራዊተ ገብርኤል ሐራ፣ አንተኑ ውእቱ ለጸሎት ጥበበ ቅዱሳን ብሔራ፣ ወአንተኑ ዘተረከብከ ለጸሎት አሠራ፡፡ | 39. ለሐቋከ፡- የቅዱሳን መከራ ሰይፍን ዘወትር በበረሓና በድንኳን ውስጥ ለታጠቀ ወገብህ ሰላምታ ይገባል፣ አባታችን አባለ ክርስቶስ ሆይ! ‹የቅዱስ ገብርኤል ሰራዊት ጭፍራ የጸሎት ጥበብ ሀገር አንተ ነህን! በጸሎት ጐዳና የተገኘህ አንተ ነህን!› ይሉሃል፡፡ |
| ፵. ሰላም ለአጻብዒከ እለ ይነብራ ደርገ፣ ዘምስለ አበው ፍጹማን ዘቤተ እንጦንዮስ ሕገ፣ አባለ ክርስቶስ ዘኮንከ መልአከ ብሥራት ዘውገ፣ በለኒ ኀጢአትከ በኀበ ፈጣሪ ተኀድገ፣ ወከመ ማየ አይኅ ብዙኅ እምኔከ ነትገ፡፡ | 40. ለአጻብዒከ፡- በእንጦንዮስ ቤት ሕግ ከፍጹማን አባቶች ጋር በአንድነት ለተቀመጡ ጣቶችህ ሰላምታ ይገባል፣ የመልአከ ብሥራት የቅዱስ ገብርኤል ወገን የሆንህ አባታችን አባለ ክርስቶስ ሆይ! ‹ኀጢአትህ በፈጣሪ ዘንድ ይቅር ተባለ፣ እንደ ብዙ የጥፋት ውኃም ከአንተ ጐደለ› በለኝ፡፡ |

| | |
|---|---|
| ፵፩. ሰላም ለአብራኪከ እለ ዘልፈ ይሰግዳ፤ ለወልደ ማርያም ድንግል ምሉዐ በረከት ወጋዳ፤ አባለ ክርስቶስ ምዑዝ ወፍትው እምጽጌ ረዳ፤ ቤዛ ይኩነነ ኪዳንከ በዕለተ በቀል ወፍዳ፤ አመ ኢታድኅን እም ዘወለደት ወልዳ፡፡ | 41. ለአብራኪከ፡- በበዓትህ እና እጅ መንሻን ለተመላ ለድንግል ማርያም ልጅ ዘወትር ለሚሰግዱ ጒልበቶችህ ሰላምታ ይገባል፤ ከጽጌረዳ ይልቅ የምትወደድና የምትጣፍጥ አባለ ክርስቶስ ሆይ! እናት የወለደችውን ልጇን በማታድንበት ቀን በመከራና በፍዳ ዕለት ቃል ኪዳንህ ቤዛ ይሁነን፡፡ |
| ፵፪. ሰላም ለአእጋሪከ ኵሎ አሚረ ዘቆማ፤ ቅድመ ገጸ ንጉሥ ፈጣሪ ሥርግወ ሞገስ ወግርማ፤ አባለ ክርስቶስ በልብ እንተ ኢያፍቀርከ ጣዕማ፤ ለዛቲ ዓለም ዘሥጋ ምልዕተ ምንዳቤ ወፃማ፤ ሕዝበ መንፈስ ቅዱስ ይብሉከ ሰዋስው ዘራማ፡፡ | 42. ለአእጋሪከ፡- ሞገስንና ግርማን ለተዋበ በንጉሥ ፈጣሪ ፊት ሁልጊዜ ለቆሙ እግሮችህ ሰላምታ ይገባል፤ ችግርንና ድካምን የተመላች የዚኽችን የሥጋ ዓለም ጣዕም ያልወደድህ አባታችን አባለ ክርስቶስ ሆይ! የመንፈስ ቅዱስ ወገኖች አንተን ‹ወደ ራማ መወጣጫ መሰላል (የሰማይ ሰዋስው)› ይሉሃል፡፡ |
| ፵፫. ሰላም ለሰኰናከ መሠረተ አባል ኵሉ፤ ዘበታሕቱ ወላዕሉ፤ አባለ ክርስቶስ ዘፆርከ ለክርስቶስ ፃማ መስቀሉ፤ በዊአከ በተዋሕዶ ውሳጤ መንጦላዕት ተህሉ፤ በሥምረተ አምላክ ስብሐት ዘሎቱ ይደሉ፡፡ | 43. ለሰኰናከ፡- በላይና በታች ያለ የአካል ኹሉ መሠረት ለሆነ ተረከዝህ ሰላምታ ይገባል፤ የክርስቶስን መከራ መስቀል የተሸከምህ አባለ ክርስቶስ ሆይ! ምስጋና በሚገባው አምላክ ፈቃድ በውሳጤ መንጦላዕት ትኖር ዘንድ በአንድነት ገባህ፡፡ |
| ፵፬. ሰላም ለመከየድከ ዘበኪደቱ ቀደሰ፤ ዘባቲ ይነብር ምድረ ተጋድሎ ሐዲስ፤ አባለ ክርስቶስ ዘኮንከ ዘባሕታውያን ርእሰ፤ ነጽረኒ ወአፍቅረኒ በከመ አፍቀርኩከ አንሰ፤ ወበከመ አፍቀርከ ወልደ ሥጋ ሰብእ ዘለብሰ፡፡ | 44. ለመከየድከ፡- የሚቀመጥባት ዐዲስ የመጋደል ምድርን በመርገጡ ለከበረ መረገጫህ ሰላምታ ይገባል፤ የባሕታውያን አለቃ የሆንህ አባታችን አባለ ክርስቶስ ሆይ! የሰውን ሥጋ የተዋሐደ ወልድን ፈጽመህ እንደወደድህ እኔም አንተን ፈጽሜ እንደወደድኩህ እየተመለከትህ ውደደኝ፡፡ |
| ፵፭. ሰላም ለአጻብዒከ ዘበአእጋር ክልኤ፤ እለ ኹሉቃተ ኮነ በአፈ ኵሉ ጉባኤ፤ አባለ ክርስቶስ በጻሕቅ እንተ ኮንከነ ረዳኤ፤ ኪያከ እንዘ ንዌድስ በዐውደ ብዙኀ ሱባኤ፤ ከንቱ ውእቱ ዘያረምም ጕርዔ፡፡ | 45. ለአጻብዒከ፡- በኹሉ አፍ የተቈጠሩ ለሆኑ በኹለት እግሮችህ ላይ ለአሉ ጣቶችህ ሰላምታ ይገባል፤ በመትጋት ረዳታችን የሆንህ አባታችን አባለ ክርስቶስ ሆይ! በብዙ ጉባኤ ዐደባባይ አንተን ስናመሰግን ዝም የሚል አንደበት ከንቱ ነው፡፡ |
| ፵፮. ሰላም ለአጽፋረ እግርከ ዘአርአሆን አዳም፤ በዐይነ ኅሊና ወነፍስ ዘሕዝበ ሥጋ ወደም፤ አባለ ክርስቶስ ሊቅነ በኀበ ፈጣሪ ሥዩም፤ ፀሩአነ ለእለ ኮነ እምነ ጸሎት | 46. ለአጽፋረ እግርከ፡- በሥጋዊና በደማዊ ሰው በነፍስ ዐይነ ኅሊና መልካቸው ለአማረ ለእግርህ ጥፍሮች ሰላምታ ይገባል፤ በፈጣሪ ዘንድ የተሾምህ አለቃችን አባለ ክርስቶስ ሆይ! ከጸሎትና ከጾም |

| | |
|---|---|
| ወጸም፤ ጸሎተ ዚኣከ ቅብዐ ይኩነኒ ዮም፡፡ | የተለየን ለሆንን ለእኛ ጸሎትህ እንደ ዘይት ይሁነን፡ |
| ፵፯. ሰላም ለቆምከ ዘአሕመልመለ ቀዲሙ፤ ከመ ዕፀ ገነት ወኤዶም ምስለ ሕዋሳት ኵሎሙ፤ አባለ ክርስቶስ ክቡር ለእግዚአብሔር በስሙ፤ ተሰመይከ ወተጸዋዕከ ኀበ ዘበክብር ተሠይሙ፤ ወአክሊለ ርእስከ ኮነት ማርያም እሙ፡፡ | 47. ለቆምከ፡- እንደ ኤዶም ገነት ዕንጨት ከሕዋሳት ኹሉ ጋር አስቀድሞ ለለመለመ ቁመትህ ሰላምታ ይገባል፤ በእግዚአብሔር ስም የከበርህ አባለ ክርስቶስ ሆይ! በክብር በተሾሙት ዘንድ ተጠርተህ ተሾምህ፤ ማርያም እናቱም የራስህ ዘውድ ሆነች፡፡ |
| ፵፰. ሰላም ለመልክዕከ ዘሠናይ አርአያሁ፤ ለእግዚአብሔር በአምሳሊሁ፤ አባለ ክርስቶስ ኀቤከ መላእክተ ሰማይ በጽሁ፤ እኂዞሙ ስቴ ሕይወት በጽዋዐ ብርሃን ዘቀድሁ እስመ ከመ ያምጽኡ ዘንተ ተአዘዙ ናሁ፡፡ | 48. ለመልክዕከ፡- በእግዚአብሔር አምሳል መልኩ ለአማረ መልክህ ሰላምታ ይገባል፤ አባታችን አባለ ክርስቶስ ሆይ! ይኽን እንዲያመጡ እነሆ ታዝዘዋልና የቀዱትን የሕይወት መጠጥ በጽዋ ብርሃን ይዘው የሰማይ መላእክት ወደ አንተ ደረሱ፡፡ |
| ፵፱. ሰላም ለጸአተ ነፍስከ ዘገሠፀ ኵሎ፤ በትእምርተ ረቂቅ ነፋስ ወበምክረ ዘአዜብ ዐውሎ፤ አባለ ክርስቶስ ባቍዕ ለእግዚአብሔር ቃሎ፤ ጸግወኒ ሕይወተ ነፍስ ዘውስተ እዴከ ሀሎ፤ እስመ ለዘፈቀድከ ትሁብ ብዙኃ ተሣህሎ፡፡ | 49. ለጸአተ ነፍስከ፡- በአዜብ ዐውሎ ምክርና በረቀቀ ነፋስ ምልክት ኹሉን ለገሠፀ ለነፍስህ መውጣት ሰላምታ ይገባል፤ በእግዚአብሔር ቃል የተጠቀምህ አባታችን አባለ ክርስቶስ ሆይ! ለወደድኸው ብዙ ምሕረትን ትሰጣለህና በእጅህ ውስጥ ያለውን የነፍስን ድኅነት ስጠኝ፡፡ |
| ፶. ሰላም ለበድነ ሥጋከ ለሰብአ ሀገር ታቦቱ፤ ማኅደረ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ሠለስቱ፤ አባለ ክርስቶስ ፀሐይ ዘለቅዱሳን ተሐቱ፤ ዘረከበ ክፍለ ብእሲ ጊዜ ዕረፍቱ ወሞቱ፤ በመንግሥተ ሰማይ ምስሌከ ብፁዕ ውእቱ፡፡ | 50. ለበድነ ሥጋከ፡- የሦስቱ የአብ የወልድ የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ ለኾነ ለሰውም ማደሪያ ለሆነ ለሥጋህ በድን ሰላምታ ይገባል፤ ለቅዱሳን የምታበራ ፀሐይ አባለ ክርስቶስ ሆይ! በሞቱና በዕረፍቱ ጊዜ በመንግሥተ ሰማይ ከአንተ ጋር ዕድልን ያገኘ ሰው ብፁዕ ነው፡፡ |
| ፶፩. ሰላም ለግንዘተ ሥጋከ በዘመንፈስ ቅዱስ አልባስ፤ እምነ ንጹሕ ሥጋከ ጊዜ ተፈልጠታ ለነፍስ፤ አባለ ክርስቶስ ኅሩይ ዘቀደሱከ እምከርሥ፤ ቡሩክ አንተ እንዘ ይብሉ በቃለ ቡራኬ ሐዲስ፤ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ፡፡ | 51. ለግንዘተ ሥጋከ፡- ከንጹሕ ሥጋህ ነፍስህ በተለየች ጊዜ በመንፈስ ቅዱስ ልብሶች ለሥጋህ መገነዝ ሰላምታ ይገባል፤ አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ በዐዲስ የበረከት ቃል ‹አንተ ቡሩክ ነህ› እያሉ ከማሕፀን የመረጡህ አባታችን አባለ ክርስቶስ ሆይ! ፈጽመህ የተመረጥህ ነህ፡፡ |
| ፶፪. ሰላም ለመቃብሪከ በውስተ ኀቡዕ ያማዕት፤ ዘበስምከ ተሰምየ ማኅደረ ንጹሕ ጸሎት፤ ውስተ እደ አምላክ ውኩፍ አባለ | 52. ለመቃብሪከ፡- በስምህ የጾም ጸሎት ማደሪያ ተብሎ ለተጠራ በተሠወረ ዋሻ ውስጥ ለሆነው |

ክርስቶስ መሥዋዕት፤ ሕጽበኒ ወአንጽሐኒ እምዘአበሳ ርስሐት፤ ኀበ ቤተ መርዓከ እባእ በብዙኀ ትፍሥሕት፡፡

፶፫. ሰላም ለትንሣኤ ሥጋከ በዕለተ ምጽአት አባይ፤ አመ ይትጋብኡ ሕዝብ እለ ውስተ ምድር ወሰማይ፤ አባለ ክርስቶስ መልአክ አምጣነ መላእክት ኀሩይ፤ አስምአኒ ቃለ ፍሥሓ አመ ዕለተ ደይን ዓባይ፤ አምጣነ ይሰብክ ወልደ ቃልከ ነቢይ፡፡

፶፬. ተማሕፀንኩ በጸሎትከ ከመ ትክፍለኒ ጸጋ፤ ጊዜ ጻአታ ለነፍስ ወጊዜ ዕረፍታ ለሥጋ፤ አባለ ክርስቶስ ሥመር እንተ ኵልነ እንግልጋ፤ ወብዕለ ሐዳስ ቤትነ ከመ ኢይኩን ንትጋ፤ በከመ ይቤ ጳውሎስ ለምሥጢር ፈሊጋ፡፡

፶፭. ነዑ ንብኪ በንስሓ ኀበ ፈጣሪ ክርስቶስ፤ እምነ ዘሥጋ ማኅደር እንበለ ትትፈለጥ ነፍስ፤ ከመ ይስአል ለነ ኀቤሁ አባለ ክርስቶስ ቅዱስ፤ ወምንተ ኢነአብስ ንብረተ ዓለም መብእስ፤ አመ በግርማሁ ኀቤነ ይመጽእ ንጉሥ፡፡

ኦ አምላክ አቡነ አባለ ክርስቶስ ዕቀበኒ ወአድኅነኒ እመከራ ሥጋ ወነፍስ ሊተ ለገብርከ….. ወትረ በኵሉ ጊዜ ወበኵሉ ሰዓት ለዓለመ ዓለም አሜን፡፡

አቡነ ዘበሰማያት…

✝ ✝ ✝

መቃብርህ ሰላምታ ይገባል፤ በአምላክ እጅ ውስጥ መሥዋዕት የተቀበልህ አባታችን አባለ ክርስቶስ ሆይ! በብዙ ደስታ ወደ ሠርግህ ቤት እገባ ዘንድ ከበደል ጉስቁልና አጥበህ አንጻኝ፡፡

53. ለትንሣኤ ሥጋከ፡- በምድርና በሰማይ ያሉ ሰዎች በሚሰበሰቡ ጊዜ በታላቅ ምጽአት ጊዜ ለሥጋህ መነሣት ሰላምታ ይገባል፤ እንደ መላእክት የተመረጥህ ነህና መልአክ አባለ ክርስቶስ ሆይ! ነቢይ እንደበትህ ወልድን ይሰብካልና በታላቅ የመከራ ቀን የደስታ ቃልን አሰማኝ፡፡

54. ተማሕፀንኩ በጸሎትከ፡- በነፍስ መውጣትና በሥጋ ዕረፍት ጊዜ ጸጋን ትሰጠኝ ዘንድ በጸሎትህ ተማፀንሁ፤ አባታችን አባለ ክርስቶስ ሆይ! የምሥጢር ምንጭ ጳውሎስ እንደተናገረ የዐዲስ ቤት ሀብታችን ጉደሎ እንዳይሆን የኹላችንን መሰባሰብ ውደድ፡፡

55. ንዑ ንብኪ፡- ነፍስ ከማደሪያዋ ሥጋ ሳትለይ ወደ ፈጣሪ ክርስቶስ ኑ፤ በንስሓ እናልቅስ፤ ቅዱስ አባታችን አባለ ክርስቶስ ወደ እርሱ እንዲለምንልን ንጉሥ ክርስቶስ በግርማው ወደ እኛ በመጣ ጊዜ በኀጢአት የዓለም ገንዘብ በምንም አንበድል፡፡

አቤቱ የአባታችን አባለ ክርስቶስ አምላክ ሆይ! እኔን ባሪያህን….. ከመከራ ሥጋ ከመከራ ነፍስ ዘወትር በየጊዜውና በየሰዓቱ አድነኝ፤ ጠብቀኝም፤ ለዘለዓለሙ አሜን፡፡

አባታችን ሆይ…

✝ ✝ ✝